የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፯
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 7
ADDIS ABABA - 30th October, 1997

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፩/፲፱፻፺ ዓ.ም.
ዕለት ደራሽ የእርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................................ ገጽ ፮፻፶፩

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 21/1997
Emergency Relief Transport Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations ........................................ Page 651

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፩/፲፱፻፺

### ዕለት ደራሽ የዕርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርእስ

ይህ ደንብ "ዕለት ደራሽ የእርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፩/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· መቋቋም

፩· ዕለት ደራሽ የእርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪· ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 21/1997 COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF EMERGENCY RELIEF TRANSPORT ENTERPRISE

These Regulations are issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definition of powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No 4/1995 and Article 47(1) (a) of public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as "Emergency Relief Transport Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 21/1997."

2. *Establishment*

1) There is hereby established an Emergency Relief Transport Enterprise (hereinafter the "Enterprise") as a public Enterprise.

2) The Enterprise shall be governed by the public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

፬· <u>ዓላማ</u>

የድርጅቱ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፤

፩· የዕርዳታ ቁሳቁስ ማጓጓዝ አገልግሎት በክፍያ መስጠት፣

፪· የዕርዳታ ቁሳቁስ ማጓጓዝ ሥራ በማይኖርበት ጊዜ ማንኛውንም የልማትና የንግድ ጭነትን በክፍያ ማጓጓዝ ፤

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ዓላማ በማያደናቅፍ ሁኔታ ማንኛውንም የማጓጓዝ አገልግሎት በመስጠት ተግባር መሠማራት ፤

፬· ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ።

፭· <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፵፮ ሚሊዮን ፶፩ሺ ፵ (አርባ ስድስት ሚሊዮን ሃምሣ አንድ ሺ አርባ ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፵ ሚሊዮን ፱፻፳፭ሺ ፲፯ (አርባ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ አምስት ሺ አሥራ ሰባት ብር) በዓይነት ተከፍሏል ።

፮· <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል ። እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ።

፯· <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ።

፰· <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ።

፱· <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Supervising Authority*

A body to be designated by the government shall be the supervising authority of the enterprise.

4. *Purposes*

The purposes for which the Enterprise is established are:

1) to render relief freight road transport services for consideration;
2) to render any development and commercial freight road services for consideration when relief freight is not available;
3) without prejudice to the purpose stated in sub Article (1) of the Article, to engage in any other transport services;
4) to engage in other related activities necessary for the attainment of its purpose.

5. *Capital*

The authorized capital of the enterprise is 46,051,040 (forty six million, and fifty one thousands and forty Birr) of which Birr 40,925,017 (forty million and nine hundred twenty five thousand and seventeen Birr) is paid in kind.

6. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

7. *Liability*

The Enterprise may not be held liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The enterprise is established for an indefinite duration

9. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 30th day of October 1997.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት·ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING INTERPRISE